# የቀድሞ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ሙት ዓመት መታሰቢያ ፕሮግራም በሎስአንጀለስ ተካሄደ።

የሎስአንጀለስ የኢፌዲሪ ቆ/ጀ/ጽ/ቤት የቀድሞው የኢፌደሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ 1ኛ የሙት ዓመት አስመልክቶ የመታሰቢያ ሥነሥርዓት እ.ኤ.አ ኦገስት 31/2013 አካሂዷል። በስነስርአቱ ላይ 150 ያህል ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ተገኝተዋል።



ምክትል ቆንስል ጀኔራል አቶ ኢሳያስ ጎታ ለተሰብሳቢዎች ፕሮግራሙን በማስመልከት ንግግር ሲያደርጉ

ቆንስላ ጀኔራል ጽ/ቤቱን በመወከል ምክትል ቆንስል ጀኔራል አቶ ኢሳያስ ጐታ በስነስርአቱ ላይ ንግግር አድርገዋል። በዚህም ክቡር ጠ/ሚ/ር አቶ መለስ ፈረንጆች «towering genious» ብለው ከሚጠሩዋቸው ታላላቅ ዓላማዊ ምጡቅ ስብዕናዎች መካከል አንዱ እንደነበሩ ገልፀዋል። በማያያዝም የክቡር ጠ/ሚ/ር አቶ መለስ ዜናዊ ዜና ዕረፍት ከተሰማ በኋላ በዓለማችን ከጥቂት አጋጣሚዎች ባሻገር ታይቶ በማይታወቅ

ደረጃ ሚሊዮኖች አልቅሰዋል፣ በእንባ ተራጭተዋል፣ በታመሙበት ጊዜም ሆነ በመስዋዕታቸው ዓለማችን ሌላ ነገር ያልተፈጸመባት እስኪመስል ድረስ ኢንተርኔትና ሚዲያው ተጣብበው አሳልፈዋል፣ ከኢትዮጵያ ሩቅ ጉረቤቶች እስከዓለም አደባባይ፣ ከጎዳና ተዳዳሪ እስከሃያላን መንግሥታት መሪዎች፣ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና ሃይማኖቶች፣ የጥቁርና የነጭ ዘር፣ ከተሜና ገጠሬው ሴቶችና ወንዶች፣ ሕፃናትና አዛውንቱ አንዱ ከሌላው ባልተለየ ሁኔታ ለክቡር ጠ/ሚ/ር አቶ መለስ ፍቅራቸውንና አክብሮታቸውን በሚጥም ቋንቋና የባለቤትነት ስሜት ገልጸዋል፣ ይህም ያለምንም ጥርጥር የክቡር አቶ መለስ ዜናዊን ምጡቅ ኢትዮጵያዊ፣ አፍሪካዊና ዓለማዊ የታላቅነት ስብዕናን የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል። ክብር ጠ/ሚ/ር አቶ መለስ ዜናዊ በዚች ምድር በነበሩባቸው ጊዚያት ካበረከቱዋቸው አስተዋጽኦዎች የሚከተሉትን ለአብነት ጠቅሰዋል።



ከተሳታፊዎች መካከል በከፊል

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ለሰው ልጆች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት የተፋለሙ መሪ እንደነበሩ፣ ዲሞክራሲያዊና በተራማጅ አስተሳሰብ የሚመራ ድርጅት የገነቡ ታላቅ መሪ እንደነበሩ፣ ጥልቅ ዲሞክራሲያዊ ጽንሰሃሳቦችንና መርሆዎችን የያዘ ሕገመንግስት እንዲጸድቅ ያደረጉ ታላቅ መሪ

እንደነበሩ፣ ብዙሃነትን በአግባቡ ያስተናገዱ የእኩልነት አራማጅ መሪ እንደነበሩ፣ ለሴቶች እኩልነት መረጋገጥ የደከሙ ታላቅ መሪ እንደነበሩ፣ የወጣቶችን ሕይወት ለመቀየር የጣሩ ታላቅ መሪ እንደነበሩ፣ በኢትዮጵያ የመድበለ ፖርቲ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደረጉ መሪ እንደነበሩ፣ በኢትዮጵያ የአዲሱ የትምህርት ሥርዓት ዋነኛ መሐንዲስ እንደነበሩ፣ ዓለም በምሳሌነት እየወሰደ ያለውን የጤና ፖሊሲ የቀየሱና ያሳኩ መሪ እንደነበሩ፣ በአገራችን የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት ሰፊ ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደረጉ መሪ እንደነበሩ፣ ቤት አልባነት እንዲያከትም ፈር ቀያሽ መሪ እንደነበሩ፣ በአገራችን የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተጉ መሪ እንደነበሩ፣ የፖሊሲ ነፃነትን ለአገራች ያጎናፀፉ መሪ እንደነበሩ፣ ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ ምላሽ እንዲሰጥ የጣሩ መሪ እንደነበሩ፣ ወዘተ ገልፀዋል።



ከተሳታፊዎች መካከል በከፊል

በመጨረሻም ታሪክ ሰሪው ሰፊው ሕዝብ መሆኑን፣ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በታሪክ አጋጣሚ የሚፈጠሩ ታላላቅ መሪዎች የሚፈጥሩት ተጽእኖ ከፍተኛ መሆኑን፣ ክቡር ጠ/ሚ/ር አቶ መለስ ዜናዊ ዓለማችን ከፈጠረቻቸው ምጡቅ መሪዎች አንዱ እንደነበሩ፣ የአገራችን የሕዳሴ ጉዞ መሐንዲስ እንደነበሩ፣ ክፉ ሞት አንድ ምጡቅ ስብዕናን ከመካከላችን የወሰደብን ቢሆንም ሥራዎቻቸው ሕያው መሆናቸውን፣

በሕይወት በነበሩባቸው ጊዜያት የገነቡት ሥርዓት በድህረ ሕልፈታቸው ወቅት በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ስልጣን በሰላማዊ መንገድ እንዲሸጋገር ማስቻሉን፣ አገራችን በሌሎች መስኮችም የለውጥ ጉዞዋን መቀጠሏን፣ ይህንን የአገራችንን ፈርጀብዙ የለውጥ እርምጃ ማስቀጠል በሕይወት ያለነው ትውልድ አደራ መሆኑን በመግለጽ፣ ሰላማዊት፣ ዲሞክራሲያዊት፣ ማህበራዊ ፍትሕ የሰፈኑባትና የበለፀጉች ኢትዮጵያን ለመገንባት ሁሉም እንዲረባረብ ጥሪ አቅርበዋል።



ተሳታፊዎች አስተያየት ሲያቀርቡ

ከታዳሚዎች ውስጥ በርካታዎቹ ግጥሞችን በማንበብና አስተያየቶችን በመስጠት ተሳትፎ ያደረጉ ሲሆን፣ በዚህም የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ህያው ስራዎችን አውስተዋል።



ተሳታፊዎች አስተያየት ሲያቀርቡ

በመጨረሻም ታዳሚዎች ባወጡት የአቋም መግለጫ የኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞ መሀንዲስ የነበሩት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ የጀማመሩዋቸውን ፈርጀ ብዙ ስራዎችን ከዳር ለማድረስ አቅማቸው የፈቀደውን ድጋፍ ሁሉ ለመስጠት ቃል በመግባት ስብሰባውን አጠናቀዋል።

